10/14/2016

# «ጅብ ከማያውቁት አገር ሂዶ ቁርበት አንጥፉልኝ አለ»

ይህን ርዕስ እንድመርጥ የገፋፋኝ፣ ሰሞኑን አረጋዊ በርሀ የተባለው፣ ማንነቱን አበጥሮ በማያውቀው ወይም ራሱን ዘወትር ማሞኘት እንደባህል በያዘው ማኅበረሰብ ውስጥ ሆኖ፣ አዋቂ፣ ሐቀኛ፣ ዕውተኛ የትግራይ ልጅ፣ መስሎ ለመታየት በማሰብ፣ እግረመንገዱንም አለሁ፣ አልሞትኩም ለማለት፣«ብርሌ ከነቃ አይሆንም ዕቃ» በሚል ርዕስ ጽፎ በድረ-ገጾች ባሰራጨው ጽሑፍ፣ እኔን ተክሌ የሻውንና አቶ ገብረመድኅን አርኣያን በስም ጠቅሶ፣«ጽንፈኞችና በሬ ወለደ ትረካ» በማለት ለንባብ ያበቃው ጽሑፍ በችልታ ወይም በዝምታ መታለፍ የሌለበት ሆኖ ስልገኘሁት፣ ለዚህ የአጸፋ መልስ የተሻለ ርዕስ ይሆናል በማለት ነው።

አረጋዊ በርሀ አምጦ የወለደውን የትግራይ ነፃ አውጭ ግንባርና ኮትኩቶ ያሳደጋቸውን ከልጅነት እስከ ዕውቀት «ብፆት» እያለ ያሞካሻቸው የነበሩትን፣ «ከመምህሩ ደቀ መዝሙሩ» እንዲሉ፣ እርሱ ባሳያቸውና በነገራቸው መሠረት ተጉዘው አገሪቱን ለብተና፣ የትግሬን ትውልድ ለጥላቻና ለመገለል የዳረጉትን፣ ከትግልና ከዓላማ አንድነት አልፎ፣ የሥጋ ወንድሞቹ በሆኑት ላይ ያዘነበውን ጥላቻና ጥቅም ቀረብኝ በሚል ስሜት ፣ራሱን እንደእውነተኛ ኢትዮጵያዊ፣ እነርሱን እርሱ ባሳያቸው መንገድ ተጉዘው የፈጸሙትን የአገር ክህደት፣ የአደባባዩን በጆሮ ዓይነት፣ ኢትዮጵያን የካዱ አድርጎ የዘበዘበውን ሳነብ፣ ለካ «ጅብ ከማያውቁት አገር ሂዶ፣ቁርበት አንጥፉልኝ አለ፤» የሚባለው እንደዚህ ዓይነት ላሉ ሰዎች ትክክለኛ መገለጫ ሆኖ ስለአገኘሁት ነው። እናም ለመልስ ምቴ ርዕስ ላደርገው ወደድኩ። በአሁኖቹ የትግራይ ነፃ አውጭ ግንባር መሪዎችና በአረጋዊ በርሀ መካከል ምንም ዓይነት ልዩነት የለም። ልዩነቱ እርሱ ያራምድ የነበረው ዐማራና ኢትዮጵያዊነትን የማጥፋት ተልዕኮ፣ የትኛው መንገድ ለግባችን ይበጀናል? ለሚለው ጥያቄ በሰጡት መልስ ፣ የአረጋዊ አቋም የተራዘመ መንገድን መምረጡ፣ የሥዬ ቡድን አቋራጭ መንገድ መምረጡ የፈጠረው አለመግባባት ተሸናፊ ሆኖ፣ ከነጓዙ ከድርጅቱ ከመባረሩ በቀር ዐማራንና ኢትዮጵያን በማጥፋት ደረጃ ልዩነት ኑሮአቸው አያውቅም። ዐማራና ኢትዮጵያን የማጥፋት ዓላማ በአረጋዊ በርሀ የተጸነሰና በተከታዮቹ የዳበረ ዓላማ ነው። ለዚህም ማሳያው ፕሮራሙና እየተሠራ ያለው ሥራ ነው።

እኔ አገጋዊ በርሀን የማውቀው፣ ከተሰደደና በበጎቹ መሀል የበግ ለምድ ለብሶ የተኩላነቱን ሥራ ሢሠራ አይደለም። የማውቀው እርሱ የፈጠረውና በዐማራና በኢትዮጵያ ጥላቻ ኮትኩቶ ያሳደገው የትግሬ ነፃ አውጭ ግንባር (ወያኔ) ከ1973 እስከ 1977 ዓም የትግራይ ክፍለሀገር ኢሠፓአኮ የርዕዮተ ዓለም ጉዳይ ኃላፊ ሆኘ በሠራሁባቸው ዓመታት ውስጥ የሚጽፉቸውን፣ የሚናገራቸውን፣ በእርሱ መሪነት የተዘጋጀውን የድርጅቱን ፕሮግራም እና በሬዲዮናቸው ያሰራጩት የነበረውን የሀሰት ድርሳን የማንበብ፣ የመስማት እና ያንም የመተንተን ሥራ እሠራ ስለነበር፣ የአረጋዊን ማንነት በሥራው አበጥሬ አውቀዋለሁ። «ጓደኛህን ንገረኝና ያንተን ማንነት እነግርሃለሁ» ነውና አረጋዊን፣ ዓላማውንና ማንነቱን ለማወቅ በእርሱ ሊቀመንበርነት ጊዜ ብቻ ሳይሆን፣ በራሱ የእጅ ጽሑፍ የተጻፈውን የ1968 ዓም የትግራይ ነፃ አውጭ ግንባርን ማንፌስቶ ማንበብ ከበቂ በላይ ማሳያ ነው።

የተሓሕት የ1968 ዓም ፕሮግራም እንዲህ ይላል።

**አንደኛ፦ መግለጫ (ት ህ ነ ኣ ድ) የመጀመሪያ እትም የካቲት ወር 1968 ዓም ብሎ በአጋዊ በርሀ የእጅ ጽሑፍ እንደሆነ በሚታመነው ባለ 39 ገጽ ፕሮግራሙ በፊደል ተራ ቁጥር (ሐ) ብሔራዊ ተፅዕኖ ከህብረተሰባዊነት ርእዮተ-ዓለም በሚለው ንዑስ ርዕስ ሥር የብሔሮች ጥያቄን እንዲህ ሲል በማያሻማ መንገድ ገልጾታል። «የብሔሮች የራስን ዕድል በራስ መወሰን ማለት ተጨቋኝ ብሔር ከጨቋኙ ብሔር የፖለቲካ መገንጠል አድርጋ ነፃ የሆነ የራሷ መንግሥት ማቋቋም ማለት ነው። የራስን ዕድል ራስ የመወሰን መብት የሚፈልጉትን መገንጠልን ያበረታታሉ። ---- የአማራ ብሔር በትግራይ ሕዝብ ላይ የምታደርገው ተፅዕኖ እንመልከት፤በኢትዮጵያ ያሉት ጭቁን ብሄሮች በተለይ ብሄረ-ትግራይ በጨቋኝዋ ያማራ ብሄር የሚደርስባቸው ተጽዕኖ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጎላና እየተባባሰ በመሄዱ በብሄሮች መካከል አለመስማማትና መጠራጠርን አስከትለዋል።»**

**ሁለተኛ፦ በዚሁ መግለጫ ተሓህት 18 ሀ ዓላማና ሥራው በሚለው አንቀጹ ሥር ወያኔ ፀረ ዐማራ መሆኑን እንዲህ ሲል ይገልጸዋል። « የትግራይ ህዝብ ብሔራዊ ትግል ፀረ-የአማራ ብሔራዊ ጭቆና፣ ፀረ-ኢምፔሪያሊዝም እንዲሁም ፀረ-ንዑስ ከበርቴአዊ ጠጋኝ ለውጥ ነው። ስለዚህም የአብዮታዊው ትግል ዓላማ ከባላባታዊ ሥርዓትና ከኢምፔሪያሊዝም ነፃ የሆነ የትግራይ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ ማቋቋም ይሆናል።» ይላል።**

ይህም ምን ማለት እንደሆነ ልብ ያለው ልብ ይበል። ይህን ነው አረጋዊ ዓይኑን በጨው አጥቦ ተክሌ የሻውና ገብረመድኅን አርኣያ ሕዝብን ከሕዝብ ለማጋጨት ያልተባለና ያልተደረገ ነገር «በሬ ወለደ» ፕሮፓጋንዳ ይነዛሉ በማለት ራሱንና ማንነቱን ክዶ፣ ከሕፃንነቱ እስከ ሽምግልና ዘመኑ ያራመደውን በመሸፈጥ «የእማየን ወደ አባየ ልክክ» የሚባለው ዓይነት ሆኖ፣ የእኔን ስም ጥላሸት ለመቀባት ያደረገው ጥረት፣ ጥላሸቱ ከእኔ ሳይሆን ፣በሕይዎት ካለ ከእርሱ ገላ፣ ካለፈም ከስሙ ጋር ተጣብቆ የሚቀረው ከአረጋዊና እርሱ ካደራጀው ድርጅት ጋር ነው። የትግራይ ሕዝብ ደመኛ ጠላትም ማንም ሳይሆን ፣አረጋዊ በርሀና የወያኔ ትውልድ ነው።

ይህን የጻፈው ራሱ ነው። ይህን የኤቨረስት ተራራ የሚያክል ገሀድ ነገር እያለና ማናቸውም ኢትዮጵያዊ የሚያውቀውን፣ «የዐማራ ገዥ መደብ» አልን እንጂ፣ ዐማራ ብለን በጠላትነት አልፈረጅንም በማለት ይክዳል። ክህደት የግሉ ባሕሪና መታወቂያው ስለሆነ ለእኔ አይገርመኝም። ይህን ጉዳይ በኢሣት እኔ፣ ግደይ ደብረጽዮንና ሰሎሞን ገብረሥላሴ ሆነን፣ ባደረግነው ውይይት ወይም ክርክር አንስቼ፣

ግደይ ለማስተባበል ሳይችል መቅረቱን አይተናል። በሌላም በኩል በዘፈናቸው ዐማራን በድፍኑ ማውገዛቸውን ግደይ አልካ,ደም። እናም የአረጋዊ በርሀ የእጅ ሥራ የሆነው የትግሬ ነፃ አውጭ ግንባር ፀረ-ዐማራና ፀረ-ኢትዮጵያ ለመሆኑ ድርጅቱ ከጽንሱ እስከ ምንኩስና ዘመኑ በዐማራውና በኢትዮጵያ አንድነትና ሉዐላዊነት ላይ የፈጸማቸው አጥፊ ሥራዎች የትግራይ ትውልድ የወደፊት መታወቂያ ሆነው የተመዘገቡ ስለሆነ፣ ይህም ከአረጋዊ ስብዕና ጋር በጥብቅ የተሳሰረ ስለሆነ፣በእርጅና ዘመኑ የተጓዘበት የጥፋት ጎዳና የኅሊና እረፍት ስለነሳው፣ ያን አስተካክለሁ ወይም አስተባብላለሁ መስሎት የዘበዘበው፣ መልሶ ወደርሱ አፈሙዙን የሚከፍት መሆኑን አለመገንዘቡ፣ የአስተሳሰብ ድህነት የተጫነው ለመሆኑ ሌላው ማሳያው ነው። ይህን አባባል የሚከተለው የበለጠ ግልጽ ያደርገዋል።

አረጋዊ እኔን በጽንፈኝነት ሲፈርጅ እንዲህ ይላል። **«የአብዛኛዎቹ ጽንፈኞች ችግር የታሪክ ድንቁርና፣ የጥላቻ ፖለቲካና የማገናዘብ እጥረት-----ያስከተለው ጣጣ ሲሆን፣ በተለይ በሕዝብና በአምባገነን መንግሥት መካከል ያለውን ሠፊ ልዩነት በቅጡ ያለመረዳት እጥረት/ ጎዶሎነት---የጽንፈኞች ፍልጎት ሕዝብንም ደርቦ ለመምታት ሲሆን፣ የናንተ ደግሞ በሕዝቡ ጉያ ተወሽቆ ለመከላከል ነው።---ጽንፈኞቹ ሥልጣን አልያዙም እንጂ፣ ከቀናቸው እንደናንተው፣ ስልጣንና ሀብቱን ማግበስበስ ተቀዳሚ ሞያቸው እንደሚያደርጉ የሌሎች ሀገራት ጽንፈኞች ዕኩይ ታሪክ ያስገነዝበናል። --የገብረመድኅንና የተክሌ የሻው``በሬ ወለደ' ትረካ ለዚሁ ዓይነተኛ ምሳሌ ነው።»**

ልብ በሉ ወገኖቼ፣ «ኤርትራ በኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ተይዛለች»፣ «ትግራይ በዐፄ ዮሐንስ አገዛዝ ዘመን ራሷን ችላ ትስተዳደር ነበር»፣ «የኢትዮጵያ ችግር የብሔር ጭቆና ነው፣ ጨቋኙም ዐማራው ነው»፣ «ትግራይን ገንጥለን የታላቋ ትግራይ ረፐብሊክ እንመሠርታለን!» በማለት ከልጅነት እስከ ሽምግልና ዘመኑ ድረስ የተናገረ፣ የጻፈ፣ ያስተማረ ነው የታሪክ ደንቆሮው ፣ ወይስ ይህ ትክክል አይደለም ብሎ የሞገተው ነው የታሪክ ደንቆሮው? ይህን እኔና እርሱን የሚያውቁን የራሳቸውን የኅሊና ፍርድ ሊሰጡበት የሚችሉበት ጉዳይ ነው።

በሌላ በኩል የጥላቻ ፖለቲካን የሚያራምደው በፕሮግራም ነድፎ፣ የትግራይን ለጋ ትውልድ በጠብመንጃ አፈሙዝ ሥር አስቀምጦ ዐማራውን በደመኛ ጠላትነት ፈርጆ፣ ነገዱን ያደራጀ፣ የመራና ያዋጋው አረጋዊ ነው? ወይስ ይህ ትክልል አይደለም፤ ዐማራው የትግሬ ነገድ ጠላት ሆኖ አያውቅም በማለት አረጋዊንና ቡድኑን የሞገትኩት ተክሌ የሻው? ለሁሉም መልሱን የትግራይ ገበሬ በግልጽ የሚያውቀው ጉዳይ ስለሆነ፣ የእኔ ችግር አይሆነም።

በሌላ በኩል አረጋዊ የቃላትን  ጽንሰ ሀሳባቸውን ብቻ ፣ሳይሆን ትርጉማቸውን የማያውቅ፣ መሆኑን፣ እኔንና ገብረመድኅንን «ጽንፈኞች» ሲል ፈርጆናል። በርሱ ቤት ታላቅ የማርክሲስት ጃርገን መጠቀሙና አንባቢየን አሳምናለሁ ብሎ አምኖ ወይም ገምቶ ሊሆን ይችላል። ይህ ጽንፈኛ የተባለው ቃል በሥራ ላይ የሚውለው፣ በአንድ አቋም ላይ በሚደረግ ውይይት ወይም ክርክር፣ የቀኙን ቀይም የግራውን የመጨረሻ ጠርዝ ለያዙ ግለሰቦችና ቡድኖች የሚሰጥ ነው። እኔ የማራምደው አቋም፣ በአረጋዊ በርሀ የተመሠረተው የትግሬ ነፃ አውጭ ግንባር ዐማራውን በአውራ ጠላትነት ፈርጆ እያጠፋው ነው፤ ይህን ጥፋት ዐማራው ተደራጅቶ ራሱን ከጥፋት ተከላከል የሚል ነው። ይህ ጽንፈኝነት ሳይሆን፣ ተከላካይነት ነው። የመከላከል ጥያቄው የተነሳውም፣ አንደኛ አረጋዊ በርሀ ጽፎ ባጸደቀው የ1968 የተሐሕት ፕሮግራም፣ ድርጅቱ የሚታገላቸውን ጠላቶቹን በቅደም ተከተል ሲመዘግብ፣ በመጀመሪያ ደረጃ የትግራይ ሕዝብ ደመኛ ጠላት«ዐማራ ነው» ብሎ ያሰፈረ መሆኑ፤ ሁለተኛው ይህን  ዐላማውን ከ1972 ዓም ጀምሮ በወልቃይት፤ ጠገዴ፣ ጠለምትና አጎራባች ወረዳ የዐማራ ተወላጆች ላይ የዘር ፍጅት መፈጸሙ፣ በማከታተልም በ1983 ዓም ሥልጣን ከያዘ ጀምሮ በምሥራቅ፣ መብዕራብ፣ በደቡብና በመሀል ኢትዮጵያ ነዋሪ በሆኑ ዐማሮች ላይ ከግድያ እስከ ማፈናቀል የደረሰ ግፍ በመፈጸሙ ነው። ይህ ጽንፈኝነት ሳይሆን፣ ተከላካይነት ነው። እናም የታሪክ ደንቆሮው ማን እንደሆነ አንባቢ ይመዝነን። «ብሳና ይነቅዛል ወይ ቢሉት፣ ለእንጨቱ ሁሉ ማን አስተማረው?» እንደተባለው፣ የጥላቻ ፖለቲካን ማን መርቶ እና አደራጅቶ ከዚህ አደረሰውና ነው፣ አረጋዊ ሌሎቹን በጥላቻ የሚከሰው። ሰዎች የዘሩትይ ያጭዳሉ፤ ዛሬ በትግራይ ሕዝብ ላይ ለሚታየው መገለልና መጠላት ዘሩን የዘራው አረጋዊና ቡድኑ መሆኑን የትግራይ ሕዝብ ያውቃል። አረጋዊ የዘራኸውን መሰብሰብ ስትጀምር ምነው ጥፋትክን ወደ ሌሎች ለማዞር ቃጣህ? «አባቶቻችን ሥራ ለሠሪው ፣እሾህ ላጣሪው» የሚሉት ይህን ዓይነቱን ድርጊት ነው። ለትግራይ መጭ ትውልድ የዘራኸው ዘር ይህ ዛሬ የምትሰማው ነው። ይህ ደግሞ ጅምር እንጂ፣ ድምድም አይምሰልህ። የታሪክ ዕውቀቱ፣ ሕዝብና መንግሥት ያላቸውን አንድነትና ልዩን ብታውቅ ኖሮ፣ ከጅምሩ ትግራይ ለመገንጠል አታስብም ነበር። ዐማራውን የትግራይ ሕዝብ አውራ ጠላት አድርገህ ፈርጀህ የትግሬ ትውልድ እንዲያጠፋው አትቀሰቅስም፣ አታዳራጅም ነበር። ዛሬም የማመዛዘን ችሎታህ ዝቅተኛ ስለሆነ፣ ያንተን ጥፋት በተክሌና በገብረመድኅን ላይ ለመላከክ ትውተረተራለህ። ሀሳብህ ግን ከትዝብት በቀር የሰው ኅሊና ዘልቆ የሚገባ ይሆናል የሚባል አይደለም።

አንባቢዎቼ ልብ በሉልኝ! አረጋዊ የማገብት( ማኅበረ ገስገስቲ ትግራይ»፣ ተሓሕት(ተጋድሎ ሓርነት ሕዝቢ ትግራይ) ሊቀመንበርና የሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራን ፕሮግራም ጽፎ ያጸደቀ ነው። ከ1967 እስከ 1971 ድርጅቱን በትጥቅ በሊቀመንበርነት የማራ ነው።ከ1971 የካቲት ወር ጀምሮ እስከ ተባረረበት ጊዜ ወታደራዊ ዋና አዛዥ ሆኖ፤ የሠራና በነዚህ ዓመታት ውስጥ ወያኔ በትግራይ ሕዝብ፣ በዐማራው እና በኢትዮጵያ አንድነት ላይ ለተፈጸሙ ወንጀሎች በመጀመሪያ ደረጃ ተጠያቂ ነው። ለምሳሌ በ1968—69 የትግራይ ክፍለ-ሀገር አስተዳዳሪ የነበሩት ዶ/ር ኃይለሥላሴ በላይ የተባሉት፣ በአረጋዊ በርሀ የሚመራውን የወንበዴ ቡድን በሽምግልና አግባብተው ወደ ሰላማዊ ኑሮ እንዲመለሱ የሚከተሉትን የአገር ሽማግሌዎች ላኩ። እነዚም፡-

1. አቶ ገብረሊባኖስ መዝገበ፣
2. አቶ ተወልደ ገብረሥላሴ፣
3. አቶ አበበ ገብረማርያም፣
4. አቶ ሙሉጌታ ደስታ፣

5. አቶ በላይ ባሕታይ፣
6. ቄስ ጽጌ፣
7. አቶ ወልደንጉሥ፣
8. አቶ ገብረጻዲቅ ፀጋይ፣
9. አለቃ ገብረሚካኤል ።

እነዚህ ሰዎች ከአስተዳዳሪው የተሰጣቸውን መልዕክት ካዳመጡ በኋላ፣ በአረጋዊ የሚመራው ዘረኛና አገርና ትውልድ አጥፊ ቡድን፣ እነዚህን ሰዎች ከለቀቅን፣ ተፈርተን ለመከበርና ሕዝቡን በቁጥጥራችን ሥር አውለን ኢትዮጵያና እትዮጵያዊነትን ለማጥፋት፣ ከሁሉም በላይ ዐማራውን ከምድረ ገጽ ለማጥፋት ላቀድነው ሠፊ ዓላማ እንቅፋት ስለሚሆን፣ እነርሱን ገድለን ሬሳቸውን ለአውሬ በመስጠት መቀጣጫ ማድረግ አለብን በማለት በአቃቂ ሁኔታ ገድለው ፣አስከሬናቸውን ጅብ እንዲበላው ማድረጋቸው ይታወቃል። ለሸዕቢያ እርዳታ ከሰላሳ ሺ በላይ የትግሬን ወጣቶች መልምሎ በሳህል በረሃ ረግፈው እንዲቀሩ ያደረገው አረጋዊ ነው። በትግራይ ነፃነት ስም ስልሳ ሺ(60,000) እንዲገደሉ፣ መቶ ሰባ ሺ (170,000) የአካል ጉዳተኞች እንዲሆኑ ያደረገው አረጋዊና ቡድኑ ናቸው። በርካታ ንፁሕ ኢትዮጵያዊ ትግሬ የሆኑትን በተከሉ ሐዋዝ አቀነባባሪነት  የሀሰት ምስክርነት ለደርግ የመረጃ መረብ እያቀበለ ያስገለ አረጋዊና ቡድኑ ነው። የትግራይን ሕዝብ ከኢትዮጵያ ለመጠነጠል፣ የሀሰት ጠላት ፈጥሮ ደም ያቃባ ነው የትግራይ ጠላት ?ወይስ የትግራይ ሕዝብ ኢትዮጵያዊ ነው? ዐማራው ወንድም እህቱ ነው ያለውን ነው የትግራይ ሕዝብ ጠላት?

በሌላ በኩል ለታላቋ ትግራይ ምሥረታ ከጎንደር እና ከወሎ የዘረፉትን መሬት በካርታው ተካቶ እኒደሠራ ያደረገው አረጋዊ ነው። በዚህም የተነሳ በወልቃይት፣ ጠገዴና ጠለምት ሕዝብ ላይ የደረሰው ግድያና ንብረት ነጠቃ፣ እስራት፣ስደትና ስቃይ አዛዡ አረጋዊ ነው። ዛሬ በሥልጣን ላይ ያሉት የርሱ ደቀመዛሙርት ለሱዳን የሰጡትን የሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያን መሬት በ1975 ዓም ላይ አረጋዊ ሥልጣን ከያዙ ለሱዳኖች አሳልፎ እንደሚሰጥ የተስማማ ሰው ነው። በ1969 የሱማሌ ወራሪ መንግሥት የኢትዮጵያን ድንበር ተሻግሮ በምሥራቅ 700ኪሜ በደቡብ 300ኪሌ በገባ ጊዜ በአረጋዊ የሚመራው ዘረኛና አገር አጥፊ ቡድን የዚያድ ባሬ ጎን በመቆም ወረራውን መረጃ በማቀበል ጭምር የረዳ ከሀዲ ነው። ለዚህ የክህደት ተግባሩም 3000 (ሦስት ሺ) ክልሽንኮቭ የተቀበለ ነው።

እታዲያ የታሪክ ደንቆሮውና ጽንፈኛው ተክሌ ወይስ አረጋዊ? ፍርድ ለአንባብያን፤